# ሽምግልና

*መልካም ሽምግልና ዘላቂ መፍትሔ ያበጃል። ደካማ ሽማግልና ግን « ገዥ ቢበድልም ተገዥ ይካስ» ይላል።*

መልካም ሽማግልና ከዳኝነት የበለጠ እውቀት፣ ጥበብ፣ ስነ ባሕርይና ታማኝነት እንዳለው ይገመታል። ይህም በመሆኑ ተቃራኒ ጉዳይ ያላቸው ወገኖች ተካሰው ለመሸናነፍ፥ ተሟግቶ ለመርታታት እስጥ አገባ የሚል ሙግት ይዘው በዳኛ ፊት በሚቀርቡበት ሁኔታ በሽማግልና ፊት አይቀርቡም። ከሽምግልና የሚደብቁት ምሥጢርም የለም። ሽምግልና የዳኝነት፥ ያባትነትና የምስክርነትና ያዛኝነት ጸጋ የተሞላው ነውና አያመሰካርም። የመልካም ሽምግልና ተልእኮ ሁለቱን የተበዳደሉ ወገኖች አቀራርቦ የሁለቱም ወገኖች ሐሳብ የጸነሰውን እውነት የሁለቱም ሕሊና ከቀበረበት ፈልቅቆ አውጥቶ ከጨበጠ በኋላ፥ እንደ ዳኛ ፈርዶ ወሕኒ ቤት አይለቅም። ይልቁንም የበደለኛውን ሕሊና ከወደቀበት የበደል አዘቅት አውጥቶ በዳኝነት ወንበር (የመንፈስ ልዕልና) ላይ ይሰይመዋል። በደለኛው እራሱ የፈጸመውን በደል በገዛ ሕሊናው እንዲገነዘበውና እራሱን ታዝቦ በራሱ ላይ የሚፈርድ ዳኛ ያደርገዋል።

የበደለኛውን ሕሊና እራሱን ከሚቃኝበትና ራሱን አይቶ ከሚታዘብበት አፋፍ ላይ ካደረሰ በኋላ፥ ወደ ተበዳዩ ፊቱን አዙሮ «አንተ በተበደልክበት በደል መስፈርት የሞላ፡ አገር የበጠበጠ፡ ወንድምህ ባንተ ላይ የፈጸመውን ያህል እጅግ የከፋ በደል ባይኖርብህም፡ ሰው ነህና አምላክህና የገዛ ሕሊናህ የሚአውቁት ሌላ ከዚህ ጉዳይ ጋር ያልተያያዘ ትንሽ በደል ሳትፈጽም አትቀርም። ይህን የማትቀበል ከሆንክ እስካሁን በዚህ ዓለም አልነበርኩም ማለትህ ነውና እንዳትሳሳት። ይህ ደግሞ ራሱ ጥልቅ ኃጢአት ነው። ይህን የበደለህን ወንድምህን ይቅር ብትል አንተና ፈጣሪህ ብቻ የምታውቁት በደልህ ይሰረይልሐል። ወደፊትም ድንገት ተሳስተህ በደል ብትፈጽም እንኳ በቀላሉ ይቅርታ ማግኘት ትችላለህ። ፈጣሪም በቅዱስ መጻሕፍ ይቅር ካላላችሁ፡ እኔ ይቅር አልላችሁም ስለሚል ተበድሎ ይቅር ማለት እንደ ክርስቶስ መሆን ነው። ቅዱስ ለመሆን ይህ እድል አያምልጥህ፥ ይቅር በማለት ለቅድስና እራስህን አዘጋጅ። ለተበደልከው ካሳ እንድታገኝ ይደረጋል። ይልቁንም ከወንድምህ እንድታገኝ እኛ ከምንተምንልህ ምድራዊ ካሳ፥ መጠንና መስፈርት የማይወስነውን ሰማያዊ ካሳ ከአምላክህ ታገኛለህ» ይለዋል።

የተበደለው ወገንም በበደለው ወንድሙ ላይ ጣቱን ቀስሮ ከንፈሩን ነክሶ ደሙን በበቀል እሳት እያፈላ አልታረቅም ከማለት ይወጣል። የራሱን ሰው መሆን በአይነ ልቡናው እየተመለከተ በበደለው ወንድሙ ጦር የተወጋው የሕሊና ቁስል እያመረቀዘ የሚፈሰውን ደም በራሱ እየጠረገ የቂሙን ቁስል ለመፈወስ ከራሱ ጋር መታገል ይጀምራል። በደለኛውም ከነበረበት አውሬነት ይላቀቅና ወደ ሰውነቱ ይመጣል። የወጋውን የወንዱሙን ቁስል መመልከት ይጀምርና የወጋበትን ጦር ከወንድሙ ልብ ላይ ነቅሎ በራሱ ልብ ላይ ይሰካዋል። በወንድሙ ላይ የፈጸመው በደል ይሰማውና ስቅስቅ ብሎ ማልቀስ ይጀምራል። የተበዳዩ መንፈስ ከወደቀበት ቂምና በቀል ዋሻ ውስጥ በመውጣት በቂምና በበቀል ጠለሸት ተሸፍኖ በነበረው አይኑ የጠላቱን የጸጸት እንባ ሰርቆ መመልከት ይጀምራል። ከእውነተኛ የሕሊና ጸጸት የሚፈልቀው የጠላቱ እንባ ሕሊናውን ሸፍኖት የነበረውን የቂምና የበቀል ጠለሸት ያጥብለትና ከቂም ከበቀል በተላቀቀ ዓይነ ሕሊናው ይመለከተዋል። የጠላቱ ንስሐ በሕሊናው ላይ ተከምሮ ያስጨንቀው የነበረውን የበቀል ወፈጥ ይሰብርለታል። በዳይም ተበዳይም ከነበሩበት የመጠቃቃት ሰመመን ይነቃሉ። ሁሉም እኩል ንጹሕ እንባ ማፍሰስ ይጀምራሉ።

በደለኛ የበደልኩት ይህን ስላደረገኝ ነው እያለ ለበደሉ ምክንያት ለመጥቀስ ከመሞከር ፍጹም ይላቀቅና የራሱን በደል ብቻ በመዘርዘር ይህን ይህን በማድረግ ወንድሜን በድያለሁ። “አበስኩ ገበርኩ ምንኛ ኃጢአቴ የከበደኝ ሰው ነኝ” ወንሜን ብቻ አይደለም ሰማዩን ምድሩን ማለትም ተፈጥሮንና ፈጣሪን በድያለሁ። የገዛ ጥርሴን በራሴ ኃጢአት እየሳልኩ የገዛ መቃብሬን ቆፍሬ እራሴን የቀበርኩ ሙት ነኝና አውጡኝ ከመቃብሬ ብሎ ድንጋይ ተሸክሞ በሽማግሌወችና በበደለው ወንድሙ ፊት ይወድቃል። የተበደለው ወገንም «እኔ ልቀበርልህ፥ እኔ ልሙትልህ» ብሎ ከበደለው ወንድሙ ትክሻ ላይ ድንጋውን ለማውረድ የሽማግልናው የአይን ቅጽበት አይቀድመውም።

ሽምግልናውም ይቅርታ ይደረግልኝ ብሎ የመጠየቁንና ካሳ የመክፈሉን ኃላፊነት ለበዳይ፥ ይቅርታ መስጠቱንና ካሳ የመቀበሉን ኃላፊነት ደግሞ ለተበደለ እንዲሆን ካደረገ በኋላ፥ ውሾን ያነሳ ውሻ ይሁን ብሎ፥ አንዱን ከፍ ሌላውን ከፍ ዝቅ ሳያደርግ ሁሉም ቅዱሳን እና ጀግኖች ናቸው ብሎ እርቁን ይፋ ያደርገዋል። በነገራችን ላይ ብዙ ባሕሎቻችን ከሙሴ መጽሐፍ የተወሰዱ ናቸው። ከብዙ ባሕላችን አንዱ ሽምግልና ነው። እንዳጋጣሚ ደግሞ የሙሴ መጽሐፍ የባሕላችን መሰረት ከመሆኑ በላይ የይሁዳዎችም፥ የክርስቲያኖችም የስላሞችም ነው። ሁሉም ከሁሉም ካልሆነ በቀር፥ ሽምግልና ቢለካበት ሁሉም የሚስማማበት ይመስላል።

ሙሴ «ተዘከር መዋእለ ትካት፡ ወሐሊ ዓመተ ለትውልደ ትውልድ፥ ተስአሎ ለአቡከ ወይነግረከ፡ ወለሊቃውንቲከ ይዜንውከ» (ዘዳ ፴፪፡፯) አለ። ማለትም "ባለፈው ዘመን ሲደረግ የነበረውን አስታውስ፥ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚሻገረውንም ባሕል አትርሳ የሚአውቀውን አባትህን ጠይቅ፥ የሚመራመረውን ና የሚአስተምረውን አዛውንትም ቅረበው ጥበቡን ይነግርሀል" ይህ የሙሴ መጽሐፍ ሽማግልና በእድሜ በእውቀት በልምድና በጥበብ ላይ የተመሰረተ እንዲሆነ የሚአሳይ ነው። ከዚህም ጋራ እንደነ መጽሐፈ ሲራክ ያሉት የብሉዩ ተረፈ መጻሕፍት ደግሞ ይህንኑ የሚአብራሩ መተርጉማን ናቸው ለምሳሌ፡-

፩ኛ «ኢትአብስ ለሰብአ ሀገርከ፡ ወኢታስህት ርእሰከ በማእከለ ሕዝብ» (ሲራክ ፯፡፯) ማለትም አገርሕን ሕዝብሕን በድለህ እትዝብት ላይ እንዳትወድቅ ተጠንቀቅ የሚለውን ያውቃል። ከግላዊ ስሜትና ጥቅም ተላቋል። እውነትን በተግባር ላይ ለማዋል የሰው አይን ፈርቶ በማዳላት የጽድቅን ሚዛን አይሰብርም። በዚህ አይነት ትልቅ ሸንጎ ላይ እራስን ዝቅ የሚአደርግ ስሕተት አይሰራም።

፪ኛ «ኢታደሉ ለገጽ እንዘ ላእለ ነፍስከ ይብጽሐከ ወኢትሕፈር ከመ ኢታውድቅ ርእሰከ» (ሲ. ፱፡፳፪) ሕሊናህ እየጨኾብሕ መንፈስህ እየመሰከረብህ እያለ ከተሳሳተ ጋር በመሰለፍ ሽምግልናሕን አታዋርድ የሚለውን ምእዳን ጠንቅቆ ያውቃል።

፫ኛ «ብእሲ ምሁር ዘተገሰጸ ብዙኃ የአምር ወዘአፈድፈደ ሕማመ ጥበበ ይነግር» (ሲራ ፴፩፡፱) እንዲል፥ ሽምግልና በዓለም ዙሪያ ያለውን ክፋውንና ደጉን አይቶ ዓለምን ንቆ የጎረጥ በማየት ላይ እንዳለ ይገመታል። ከውሸት ከማስመሰል መንኖ የራቀ ለመምከርና ለመገሰጽ በቅቶ እውነትንና ሐሰትን የማይቀላቀል እንደ ሶቅራጥስ እና እንደ ክርስቶስ «ወጽድቅኒ ታግእዘክሙ» ለማለት የበቃ እንዲሆን ይጠበቅበታል። እኒህ ካንድ እስከ ሶስት የተገለጹት የሽምግልና ባሕርያት፥ በጎና የተቀደሰ የማይዝገው ያገራችን ሽምግልና የተመሰረተበት ነው። በተቃራኒው ደግሞ የሽምግልና ሚዛን የጎደለው ሽማግልናም አለ። እንመልከተው።

ጥበብ የጎደለው ሽምግልና ዘላቂ ሕልም የለውም። እንዲአውም ዘላቂ ሕልም  የሚቀብር ነው። ከፊቱ ካለው ችግር አርቆ ቀዋሚና መሰረታዊ መፍትሔ አያስብም። ለዚህም ደካማ ሽምግልና አባቶች ሶስት ሰዎችን ሮቤልን፡ ይሁዳንና  እና የሮብዓምን ሰወች እንደምሳሌ ይጠቅሳሉ። ታሪኩ በቅዱሱ መጽሀፍ ላይ የተመዘገበው ነው። በወንድማማቾች መካከል ችግር ተፈጠረ። ራዕይና ሕልም ያለውን ወንድማቸውን ዮሴፍን ለመግደል ወሰኑ። ሮቤል የተሻለ አስታራቂ የሽምግልና ሐሳብ አመጣ። ያም ሐሳብ ዮሴፍን ጉድጓድ ውስጥ መጣል ነበር። ይህ አይነት ሽምግልና ለጊዜው ከሞት ያዳነ የተሻለ ሽምግልና ነው። ነገር ግን ከሞት ያዳነ ሽምግልና ቢሆንም፥ ያንኑ የተበደለውን ወንድም በሕይወት እያለ ቁሞ እየሄደ የሚቀብር ሽምግልና ይሉታል። (ዘፍ ፴፯፡፳፪)  ሌላው የይሁዳ ሽምግልና ነው። ይህ ሽምግልና ዮሴፍን በሕይወቱ እያለ እዚያው ተቀብሮ እንዳይቀር ከጉድጓድ አውጥቶታል። ነገርግን እንደገና የመተያየትና የመገናኘት ተስፋ በማያሰይ ሁኔታ ያንኑ የተበደለውን ወገን ለባርነት የሸጠ ሽምግልና ነው ይሉታል። (ዘፍ ፴፯፡፳፯) ሶስተኛው በሮብአም ዘመን የታየው ሽማግልና ነው። (ዜና ፲፡፯) ያገዛዝ ቀንበር በከበዳቸውና በገዥው በሮብዓም መካከል በተነሳው ችግር፡ ጥበብ ከጎደላቸው ሽማጌሌወች የመጣው የመፍትሔ ሐሳብ (ታናሽቱ ጣቴ ካባቴ ወገብ ትወፍራለች፥ አባቴ ከጫነበችሁ በላይ እጨምርባችኋ። አባቴ ባለንጋ ይገርፋችሁ ነበር። እኔ ግን በጊንጥ እገርፋችኋለሁ በላቸው) የሚል ነበር። ይህ ሽምግልና በሮብዓምና በሕዝቡ መካከል የነበረውን ጸብ አጋግሎ  የሮብአምን መንግሥት አፈረሰ። እንዲአውም ጭራሽ ሮብአምን ካገሩ ተሰዶ እንዲጠፋ አደረገ። (ዜና መዋእል ፲፡፲፰)

እንደዚሁም ሁሉ በአገራችን ጥበብ የጎደለው፥ እርቀ የማያስብና መሰርት የለሽ ሽምግልና እንዳለ ይነገራል። ለምሳሌ ሶስቱን ብቻ እንመልከት፡-

፩ኛ፡- ራሱ ገርፎ እራሱ የሚጮህ የጅራፍ ባሕርይ ያለው አምባ ገነን ሆኖ ሕዝቡን ሲበድል፥ ያገር ሽማግሌወችም በጥቅም ተደልለው፥ ወይም መንፈሳቸውን በፍርሐት ሰብረው የበደለውን አምባ ገነን ከመገሰጽ ይልቅ «የበደለ ገዥ ነው፡ ግን ተገዥ ይካስ» የሚል ሽምግልና ነው። እዚህ ሽምግልና ላይ ሳናስተውለው ልናልፈው የማይገባ ነገር አለ። ይህ ሽምግልና “የተበደለ ተገዥ ነው። አንድ ጊዜ ተበድሏል መበደልም ልማዱ ነው፡ ካሳ መክፈልም ልማዱ ነውና መቼስ ምን ይደረግ ያው የተበደለው ተገዥ ይቅርታ ይጠይቅ፡ ካሳም ይክፈል” ብሎ ያንኑ የተበደለውን ወገን ሁሉን ተሸካሚ ቢአደርግም፥ መበደልና ካሳ የመቀበል ልማድ ደግሞ የባለስልጣን ነውና ገዥው ይቅር ይበል። ካሳውን ይቀበልና ሰላም ይውረድ» በማለቱ ሽምግልናው ቢሸመደመድበትም፥ ሹሙ የበደለ መሆኑን አልደበቀም ቅዱስ ነውም አላለምና ይህ አይነቱ ሽምግልና በከፊልም ቢሆን ይሻላል።

፪ኛው የደብረ ሊባኖስ መነኮሳት ቀብተው በሚአነግሡበት ዘመን ተደረገ እየተባለ ሲነገር የምንሰማው ነው። አጼ ምኒልክና ወንድማቸው ልጅ ታየ እኔ እነግሥ እኔ እነግሥ ሲፎካከሩ ሁለቱም በየተራ ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም ሄደው ቢነግሱ የገዳሙን ውለታ እንደማይረሱና የገዳሙ ሰወች በጸሎታቸው እንዲአስቧቸው በየተራ ሄደው ተማጸኑ። የገዳሙ ሰወች እውነቱን ከመንገር ይልቅ ሁለቱንም እሽ እያሉ ከሸኙ በኋላ፥ ወደ አጼ ምንይልክ አዳልተው «አጼ ምኒልክን ከዙፋኑ አያናውጥ፥ ልጅ ታየ ዳርዳሩን ያነጥንጥ፥ ይቀበለው እግዚአብሔር አቡነ ዘበሰማያት» አሉ የሚባለው ነው። ይህ አይነቱ ሽምግልና የራስን መንፈሳዊነት ዝቅ ያደረገ። የእግዚአብሔርንም ስም ለራስ ሽፍጥ የተጠቀመ። ልጅ ታየን ያታለለ ሽምግልና ይሉታል።

፫ኛው ባሏ የፈታት የቤት እመቤት የኔ ቢጤ ተዝካር የለመዱትን ቄስ እባክዎ ከባሌ ያስታርቁኝ አለቻቸው። ጉዳዩን በተስተካከለ ሽምግልና ሳይፈጽሙላት ተዝካሩ ትዝ አላቸውና «ፍታት» ብለው ሄዱ። እሷም የታመነባቸውን የሽምግልና ስራ ባለመስራታቸው ቅሬታዋን «ምን ያሉ ቄስ ናቸው ተዝካር የለመዱ፥ ያስታርቁኝ ብላቸው ፍታት ብለው ሄዱ» ብላ የከሰሰችው የቄሱ ሽምግልና ነው። ይህ ሽምግልና ተልእኮውን የሳተ፡ ሳምባ እንጅ ልብ የሌለው ሆድ አምላኪ ሽምግልና ይሉታል።

እንግዲህ የሐገራችን ሽምግልና እንዲህ የተሸመደመደ እና፥ እንዲያ የተቀደሰ ገጽም አለው። ዛሬ በአገራችን የታወጀው ሽምግልና የትኛውን አቅጣጫ እንደተከተለ በግልጽ መረዳት እንችል ዘንድ ክፉውን ገጽና በጎውን ገጽ አብረን ልንመረምረውና ልንመዝነው ይገባል። ወንጀል ሳይፈጽሙ መንግሥት በደለን በማለታቸው ብቻ ኢትዮጵያ እምጣ የወለደቻቸው በየወሀኒ ቤቱና በየፖሊስ ጣቢያው ታስረው በመሰቃየት ያሉት ሁሉ መበደላቸው አንሶ ገዥን አጎብድደው ይቅርታ እንዲጠይቁ ህሊናቸውን መፈታተን ሽምግልና ነወይ? የራሱን ሕዝብ የሚፈጅን ገዥ የዉጭ ሐይላት እንዳይረዱ በአገራችን ምሁራን የቀረበውን ሰነድ ለማጨናገፍ የሚዳዳ ሽምግልና እዉነት ሽምግልና ነወይ? እዉነት ይህ ሽምግልና በግፍ የተገደሉትን፣ የታሰሩትና የተሰቃዩትን በበዳይነት ፈርጆ ከሆነ «አንች አገር እኔን የወለድሽን እንደ ጣሊያን ከመሰለ ባእድ ጠላትሽ ጋር ሰዋጋ እንድሞት ይመስለኝ ነበር፥ እኔን አምጠሽ በወለድሻቸው ልጆችሽ በገዛ ወንድሞቼ እጅ ታንቄ እንድሞት ከፈረድሽብኝ እንደኔ ያለ ወንድ አይወለድብሽ» ብሎ እንባውን እየረጨ ወደተሰቀለበት መስቀል ተወሰደ ሲባል እንሰማለን። ሽምግልናው ዛሬም ይህ እንዲቀም አይፈልግም ማለት ነው? አሁንም የጀግኖች ኢትዮጵያውያን እንባ በነበረው ሁኔታ እየፈሰሰ እንዲቀጥል ይፈለጋል ማለት ነው? አንዳንድ ጊዜ ሽማግሌ ዋሽቶ ያስታርቃል ቢባልም በተበደለው አካል ላይ ሁልጊዜ በደል ተሸካሚ አርጎ የሚወስን ከሆነ ተጠቂው የታሰረበትን ገመድ የፈታ አስመስሎ በማላላት ያንኑ ተጠቂውን ማስደብደብ ወቀቶች ሲገጥሙ ስሕተት የሆኑትን ነገሮች እንደ አማራጭ አድርጎ ለመውሰድ ሁኔታ ያስገድዳል። ይሁን እንጅ ተገዳጁ አስገዳጁን ሁኔታ ባጥጋቢ ማስረጃ የማስረዳት የስነ-ምግባራዊ ግዴታ ሐላፊነቱን መውሰድ ግድ ይኖራል እንዳለው፥ ቅድስናን ለበደለው ክፍል ለመስጠትና ለበዳይ ጥብቅና ለመቆም ሽምግልናው ተገዶ ከሆነ፥ አስገዳጁን ምክንያት ለባለ ጉዳዩ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አስረድቶ እንዲቀበለው ማድረግ ስነ-ምግባራዊ ግዴታ ይመስለኛል።

ይህ ሁሉ ይሁንና፥ ኧረ ለመሆኑ የታሰሩት ወገኖች ነበሩ እንዴ ወታደሮችን አዘጋጅተው ሕዝብ ያስጨፈጨፉት? የታሰሩት ነበሩ የሕዝቡን ሕልምና ራእይ ሕዝቡ ወደ አልተመኘው አቅጣጫ የቀየሩት? የታሰሩት ነበሩ ሕዝብ ሳይመርጣቸው ከዱር መጥተው ከየአምባቸው ተጠራርተው የጋዜጠኞችን ብእርና ወረቀት ካሜራቸውን የነጠቁ? የታሰሩት ነበሩ ግማሹን እስር ቤት ግማሹን ከአገር እየወጣ እንዲሰደድ ያደረጉት? እስካሁን ኢትዮጵያውንም ፈረንጆችም በደል ፈጸሙ እያሉ የሚከሱት የታሰሩትን አይደለም። አልነበረምም። ሽምግልናው እንዴት ቅዱስ የሚለውን ቅጽል ላሳሪው ለደብዳቢው ሰጠ? ቅዱስ የሚለው ቃል «ኩኑ ቅዱሳነ እስመ ቅዱስ አነ» እያለ ከተናገረው ከፈጣሪ አፍ የወጣ እንደሆነ መጽሐፉ ይናገራል። ታዲያ ይህ ሽምግልና ቅዱስ ያለው አካል አምላክን ለመምሰል ሊሞክር ቀርቶ የአምላክን ሕልውና የሚአምን ነውን? ይህ ወቅት የታሰሩትን ለማስፈታት የተራቡትን ለማብላት፥ የታመሙትን ለመጠየቅ በቅዱሱ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ምለው በተቀደሰው ቦታ የተቀመጡትን ፓትርያርክ ባላቸው ንክኪና በራሳቸው ሽፍጥ ዓለም በራሱ ይሸከማቸውም፥ በጀርባው ይዘላቸውም የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደሆነ ቅዱስ የሚለውን ቅጽል ላለመስጠት የነፈገበት ወቅት ነው። ታዲያ ይህ ሽምግልና ቅዱስ የሚለውን ቅጽል ለመንግሥት በመስጠት ከመላ ኢትዮጵያውያን ስሜት በእጅጉ የራቀ አልሆነም ወይ?

ከላይ እንዳልኩት ትክክለኛ ገጽ ያለው ያገራችን ሽማግሌ «መታረቅ ይሻላል የበደለ ክሶ፥ ይጥላል በረዶ መብረቅ ተንተርሶ» የሚለውን እየጠቃቀሰ የበደለ ድንጋይ ተሸክሞ ይቅርታ እንዲጠይቅ፥ የተበደለ ተክሶ ይቅርታ እንዲአወርድ ያደርጋል። በዳይም ሆነ ተበዳይ ከዚሁ ባሕላችን የመጡ ስለሆኑ ሁሉም ለባሕሉ ይታዘዛሉ። የበደለ ድንጋይ ተሸክሞ ስለ እግዚአብሔር በድያለሁና ይቅር በለኝ የሚለው በተግባሬ ሙት የሆንኩ፥ በአገር ሽማጌሌወች ፊት የተጋለጥኩ ሕብረተ ሰቤ በሕሊናው ታዝቦ የቀበረኝ ነኝና እራሴን ከቀበርኩበት መቃብሬ ስለ ፈጣሪ ብላችሁ አውጡኝ ብሎ ከልቡና ካንጀቱ ስቅስቅ ብሎ እያለቀሰ መቅረብ ነው። ተበዳይም መበደሉን በዚያችው ደቂቃ ሰርዞ ሕሊናውን ከቂም ከበቀል አንጽቶ «ስለ እግዚአብሔር ይቅር ብያለሁ እኔ ልውደቅልህ ልቀበርልህ» እያለ ፈጥኖ ሮጦ ድንጋዩን ከትከሻው ላይ ያወርድለታል። በዚህ አይነት በሚፈጸመው ሽምግልና የሚከፈለው ካሳ ካንጀት ፈንቅሎ በሚወጣ እንባ የታጀበ የይቅርታ ጥያቄ ነው። የበደለውንና የቆሰለውን የወንድሙን ሕሊና ለመፈወስ የተሰበረ መንፈስ ማሳየት ነው። ሽምግልና ሁለቱን ጸበኞች ገድቧቸው የነበረውን የጸቡን አጥር ከመካከላቸው አፍርሶ በወንፈሉ በደቦው እየተረዳዱ አብረው እንዲኖሩ፡ አንዱ ባንዱ ላይ የነበረውን ጥርጥር በመተማመን ተክቶ በነሱ ላይ ጉዳት ለማድረስ ከውጭ በሚመጣው የጋራ ጠላታቸው ላይ ኃይላቸውን እንዲአስተባብሩ ማድረግ ነበር። በዚህ አይነት ሽምግልና እርቅ ከተፈጸመ በኋላ ወደኋላ ተመልሶ ይህን ጉዳይ ያነሳ ትፋቱን የሚልስ ርኩስ ውሻ ይባላል በሚለው ባሕላዊው መሐላ ሁለቱንም እኩል ማሰር ነበረበት።

ነገር ግን አሁን በእርቁ «ቅዱስ ነው» የተባለው ወገን እንኳን በበደሉ ተጸቶ የቀሩትን እስረኞች ሊፈታ፥ ወደ ትፋቱ ተመልሶ ተፈቱ የተባሉትን «ይቅርታ ጠይቀን ተፈታን ካላሉ መልሼ አስራለሁ» አለ እየተባለ በሰፊው እየተወራ ነው። ይህ እውነት ከሆነ «ቅዱስ ነው» የተባለው ወገን ትፋቱን መልሶ በመላሱ አረከሰም ወይ? ወይም ሽምግልናውን ትክክለኛውን ሚና የሳተ አላስመሰለውም ወይ? ታስረው ከተፈቱት መካከል ባንድ ወቅት «አገራችን ከትልቅ አዳጋ ላይ የወደቀችው ሽማግሌና መንፈሳዊ ሰው ማጣቷ ነው» ያሉት አነጋገራቸው በታሪክ መጽሐፋችን ትልቁን ምዕራፍ እየያዘ ነው ማለት ነው። ሽምግልና ትእቢተኛውና እብሪተኛው በትቢቱና በእብሪቱ የፈጸመውን ሁሉ በደል በራሱ ሕሊና እንዲሚለከተው እና እንዲጸጸት ከተቀመጠባት የዛሬዋ ወንበር እራሱን ዝቅ በማድረግ ወርዶ፥ ለዘላለም ጸንቶ በሚኖረው በከፍተኛው የሕሊና ልዕልና ወንበር ላይ እራሱን እንዲአስቀምጥ መርዳት ነበር። ይህ የዘመናችን ሽምግልና ይህ እንዲፈጸም አድርጓልን? የታሰሩትን ጥቂት ወገኖች እንዲፈቱ ቢአደርግም፥ ከመገደል አድኖ በጉድጓድ እንዲወድቁ ያደረገውን የሮቤልን ሽምግልና ይመስላል። ከወደቁበት ጉድጓድ ወጥተው ታርቀው በአራቸው አንድ ላይ በእኩልነት ከመኖር ይልቅ ቀዋሚ መፍትሔ ያመጣል ተብሎ የቀረበውን ቢል ለማበላሸት መሞከሩ የተገዥነትን መንፈስ የሚሰብክ፥ የተማረውን የአገሪቱ ልጆች መንፈስ ከአገሪቱ የሚአርቅ፥ እውቀታቸውንና ጥበባቸውን ሕልማቸውን በአገራቸው እንዳያውሉት የሚአደርግ ዮሴፍን ለግብጽ ነጋዴወች የሸጠውን ይሁዳን ሽምግልና አላስመሰልም ወይ? (ይህን ከበድ ያለ ምሳሌ በመጠቀሜ የሽምግልና ምንጭ የሆነውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ እጠይቃለሁ) በተበዳይና በበዳይ መካከል

የነበረውን እውነት አድበስብሶ የቅድስናን ትርጉም ገልብጦ በማለፉ፥ ሁለቱም ተበዳይና በዳይ በአገራቸው አብረው ተቃቅፈው የርኅራሄና የቅርታ እንባ እንዲአለቅሱ፥ አንዱ የሌላውን እንባ እንዲአብስና መሰረታዊው እና ለዘላቂው ኑሮ ያበቃቸው ሽምግልና አይመስልም። እንዲአውም የታረቁትን ወገኖች እኩልነት በማያሳይ፥ በማያቀራርብ ሁኔታ ላንዱ ቅድስናን ለሌላው ጀግንነትን በመስጠት እጅግ አራርቋቸዋል። መቸም በዳይና ተበዳይ እንዳለ ሁሉም ያወቀውና የሚሰወር ነገር አይደለም። ታዲያ ይህ የታወቀ ከሆነ በደለኛው የበደለውን ወንድሙን በጸጸትና በተሰበረ ሕሊና ሆኖ ካንጀት በሚወጣ እንባ የታጀበ ይቅርታ ካልጠየቀ አድበስብሶ ማለፍ በደለኛውና እብሪተኛው ባለበት ጸንቶ እንዲቀጥል ማድረግ አይመስልምን? በተቃራኒው ደግሞ በደለኛ ይቅርታ ተጠያቂ እና ካሳ ተቀባይ ከሆነ። የተበደለ ይቅርታ ጠያቂና ካሳ ከፋይ ከሆነ «የበደለ ሹም ነው፥ ነገር ግን ባላገር ይካስ» አለ የሚባለውን የሽምግልና አይነት የተከተለ አይመስልምን? አምላክ ለኢትዮጵያ ምን እንዳዘጋጀላት አናውቅም። በዚህ አይነት ሽምግልና ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ «ገዳም ገባች አሉ ደብረ ሊባኖስ፥ ሰው እየገደሉ ይማራል ወይ ነፍስ» እያለ ከማንጎራጎር የሚወጣ አይመስልም።

ታዲያ ነገሩ ሁሉ እንዲህ ከሆነ መፍትሔው እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ እራሱን የተሻለ ሽማግሌ ለማድረግ ኢትዮጵያ ያለችበትን ሁኔታ፥ ባሕሉን፥ መጻሕፍትንና ራሱን መርመር ሊኖርበት ነው። የዘመናችን ሽምግልና ጉድለት አሳየ ብንልም ከጉድጓድ ያወጣውን የሮቤል ሽምግልና ያህል ሽምግሏል። ከጉድጓድ ያወጣውን ሮቤልን ሽምግልና መንቀፍ ብቻ ሳይሆን፤ እኛ ደግሞ ከጉድጓድ የወጣውን ሕልምና ራእይ ለሽያጭ ላለማቅረብ ይሁዳን ላለመሆን መጠንቀቅ አለብን። አባቶች «ሰው ማለት፥ ሰው የሆነ ነው ሰው የጠፋ ለት» እያሉ የሚደግሙትን ዳዊት አንርሳ። እያንዳንዳችን ኢትዮጵያውያን ይህን ተገንዝበን እውነትን መመሪያ በማድረግ፥ ለራሳችን አገርና እና ለወገናችን ቀዋሚ መፍትሔ ለመፍጠር መዘጋጀት አለብን። እርስ በራሳችን በመነጋገርና በመወያየት እራሳችንን ወደ ተሻለና ወደ በለጠ ሽማግሌነት መለወጥ አለበን።

ሁላችንንም እግዚአብሔር ያሽምግለን!

ቀሲስ አስተርአየ

ነሐሴ ፲፩ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ/ም